## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

**የሕንጻ ኮሚቴ አባላት አጭር ስብሰባ**

የሕንጻ ኮሚቴ አባላት ለአጭር ስብሰባ ከፕሮግራም በኋላ ወደ ኋላ እንድትቀሩልን በማክበር እንጠይቃለን። ጌታ ይባርካችሁ!

**በችካጎና አካባቢው ለምትገኙ አብያተክርስቲያናት በሙሉ**

**ታላቅ የመነቃቂያና የአገልጋዮች ስልጠና በቺካጎ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን**

**ቀን፡** ቅዳሜ July 29, 2017

**አገልጋይ፡** ፓስተር ዶር ቤዛለም

**ርዕስ፡** መጽሀፍ ቅዱሳዊ አመራር

**ቦታ፡** በቺካግ የምስራች ቤተ ክርስቲያን

በተጨማሪም አርብ (July 28) ከ7p.m. ጀምሮ እሁድ (July 30) ከ1፡30p.m. ጀምሮ ባለው የቤተክርስቲያኒቱ መደበኛ ፕሮግራም ላይ ያገለግላል።

**ኑ የእግዚያብሄርን ህዝብ ወደታየለት የህይወት ከፍታ እናድርስ!**

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኝት፡-**
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

**ኑ የእግዚያብሄርን ህዝብ ወደታየለት የህይወት ከፍታ እናድርስ!**




"ሁላችን የእግዚያብሄርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመስራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።" (ኤፌ. 4፡12)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | **መደበኛ ፕሮግራሞች**<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.<br>አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m. |
|---|---|
| **July 23, 2017** | **ሐምሌ 16፤ 2009 ዓ.ም.** |

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም መኮንን ጂኔሎ |
| አምልኮ........................ | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም  ብረሃኑ አንበሴ |
| ቃል ............................ | ወንድም ዮሴፍ (ከሚልዋኪ መድኃኒአለም ቤተክርስቲያን) |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## የሳምንቱ ጥቅስ

**"ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ... እግዚአብሔርም በጃንደረቦቹ አለቃ ፊት ለዳንኤል ሞገስንና ምሕረትን ሰጠው።"**

(ዳን ኤል 1፡ 8-9)

### ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተዋል?

1) እግዚአብሔር ስለሚያፈቅረን ለሕወታችን አስደናቂ እቅድ ሰጥቶናል::

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3፡16

2) ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክነያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ሮሜ 3፡23

3) ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐንስ 14፡6

4) ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐንስ 1፡12

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ፭ -- እረኞች

*"እርሱም ... ሌሎቹም እረኞች... እንዲሆኑ ሰጠ።" (ኤፌ. 4፡ 11)*

እረኛ ወይንም መጋቢ የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉም መንጋን የሚያግድ ወይንም የሚጠብቅ ማለት ነው። ይህ ደግም አንድን ለመንጋ የሚያስፈልገውን ጥበቃና ጥንቃቄን የሚያደርገውን አገልጋይ ይወክላል። ከመዝሙር 23 ላይ እንደምናስተውለው እረኛ ይመግባል፣ ይጠብቃል፣ ይመራል፣ ያሰማራል። በተጨማሪም በዮሐንስ 10፡11 ላይ እንደምናነበው ጌታ ኢየሱስ እራሱን "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" በማለት ገልጿል። ከክፍሉ እንደምንረዳው መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ መንጎቹ አሳልፎ ይሰጣል። መልካም እረኛ በጎቹን ለጠላት አሳልፎ አይሰጥም። ይልቁንም ከተኩላውና ከበላተኛው እየተናጠቀ ያድናቸዋል። መንጎቹንም ፊት ቀድሞ ይመራቸዋል። በጎቹም ድምጹን ያውቁታልና ይከተሉታል። እንግዲህ የእረኝነት አገልግሎት በጌታ ኢየሱስ እንደተገለጸው አይነት የመልካም እረኛ አገልግሎት ነው።

እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብም የእስራኤል እረኛ በሚል ምሳሌ ተገልጿል። ኢሳያስ 40 ላይ እንደተጻፈልን እግዚአብሔር "መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል።" (ቁ. 11) ከዚህ ክፍል የእረኝነት አገልግሎት በብዙ ርሕራሔ እና የመንጋውን ሁኔታ እየተመለከቱ የሚከናውን አገልግሎት እንደሆነ እንረዳለን። እረኛ መንጋውን እያስቸኮለ አይመራም። የሚሰማሩትን ያሰማራል፣ ግልገሎቹን በብብቱ ይሸከማል፣ የደከሙትን ያበረታል፣ የሚያዝኑትን ያጽናናል። በሌላም ስፍራ (ከሽማግሌዎች አገልግሎት ጋር በተያያዘ መልኩ) እንደምናነበው የእረኛ አገልግሎት በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተዋጀችውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ ነው።

እረኞች በዋናነት በአጢቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ መጋቢዎች ናቸው። አንዳንድ ሰዎች የእረኞችን አገልግሎት በቀለበት ጣት ይመስሉታል። ምሳሌው እረኞች ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸውን ቁርኝትና የአግለግሎታቸውን ማዕከል የት መሆን እንዳለበት ያመለክታል። ልክ በትዳር ያሉ ወንድና ሴት ተጋቢዎች በቀለበት እንደሚተሳሰሩ ሁሉ እንደዚሁ እረኛው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የተሰጠ ነው። በመሆኑም አገልግሎቱ እንደ ሌሎቹ ስጦታዎች ተዘዋዋሪ ሳይሆን በዋናነት በአንድ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ምእመናንን የመመገብ፣ የማሳደግ፣ የመንከባከብና የመምራት አገልግሎት ነው።